በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 215250
ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. ጋሊ አባሳንቢ
2. ቲጃኒ አባሳንቢ } አልቀረቡም

ተጠሪ፡- በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዓቃቤሕግ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ጥቅምት 02 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 35449 ሐምሌ 22 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኮንታ ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካቾች እና በስር 1ኛ ተከሳሽ ላይ በስር ፍ/ቤት አሻሽሎ ያቀረባቸው ክሶች ሰባት ሲሆኑ ይዘታቸውም፡-

1ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና አንቀጽ 323 ድንጋጌን በመተላለፍ በኮንታ ልዩ ወረዳ በቂራሪ ቀበሌ ውስጥ በቀን 11/07/2011 ዓ.ም ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት አካባቢ በጋራ በመሆን ቆጭበሬ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በሚባል መንደር የነበረውን የአካባቢውን ጸጥታ ለመቆጣጠር የሄዱትን የፖሊስ አባላት ለግዜው ካልተያዙ ግብረአበሮቻቸው ጋር በመሆን በድንጋይ በመደብደብ ስራ እንዳይሰሩ ያደረጉና የስራ ግዴታን በማይገባ ሁኔታ እንዲጣስ ማስገደድ ወንጀል ፈጽመዋል፡፡

2ኛ.ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና 324 ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በተገለፀው ልዩ ቦታ፣ቀንና ሰዓት ስራቸውን በማከናወን ላይ ባሉ የፖሊስ አባለት ላይ ጥቃት ፈጽመዋል፡፡

3ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና 333(2) ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛው ክስ በተገለፀው ልዩ ቦታ፣ቀንና ሰዓት ወታደራዊ ትዕዛዞች እንዲጣሱ በማድረግ ሌላውን ሰው የማነሳሳት ወንጀል ፈጽመዋል፡፡

4ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1(ሀ) እና አንቀጽ 337 ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በተገለፀው ልዩ ቦታ፣ ቀንና ሰዓት በፖሊስ አባላት የሀሰት ወይም የሚያደናግር መረጃ ማሰራጨት ወንጀል ፈጽመዋል፡፡ 5ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና 485 ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛው ክስ በተገለፀው ልዩ ቦታ፣ቀንና ሰዓት በወሬ ህዘብን የማሸበር ወንጀል ፈጽመዋል፡፡

6ኛ ክስ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና 486 ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛው ክስ በተገለፀው ልዩ ቦታ፣ቀንና ሰዓት የሀሰት ወሬዎችን በማውራት ሕዝብን ማነሳሳት ወንጀል ፈጽመዋል፡፡ 7ኛ ክስ፡- የስር 1ኛ ተከሳሽና 2ኛ አመልከች ብቻ የንግድ ፈቃድና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49/2/ ድንጋጌን በመተላለፍ ከ2002 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ የጸና የንግድ ፈቃድ ሳይኖራቸው ንግድ መነገድ ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡

አመልካች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ክሱን እንደማይቃወሙ ገልጸው የእምነት ክሕደት ቃላቸውንም ሲጠየቁ ድርጊቱን አልፈጸምንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ፍርድ ቤቱ የዓቃቤሕግን ማስረጃ ከሰማ በኋላ ዓቃቤሕግ እንደክሱ አስረድቷል በማለት አመልካቾች በተከሰሱበት የወንጀል ድንጋጌ እንዲከላከሉ ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካቾችም መከላከያ ምስክሮቻቸውን አስቀርበው አሰምተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካቾች ያቀረቧቸው ምስክሮች ከሌሊቱ 9፡00 ሰዓት ስለተፈጸመ ወንጀል እንጅ ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት ስለተፈጸመው ወንጀል የማያውቁ መሆኑን፣ የስር 1ኛ ተከሳሽና የአሁን 2ኛ አመልካች ሀገ-ወጥ ንግድ ስለመነገዳቸው በዓ/ህግ ምስከር የተረጋገጠባቸውን አመልካቾች ያላስተባበሉ መሆኑን ገልጾ የስር 1ኛ ተከሳሽን በ1ኛ፣3ኛ፣4ኛ፣6ኛና 7ኛ ክስ ጥፋተኛ በማድረግ በ 9 ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 10000 / አስር ሽህ / 1ኛ አመልካችን በ1ኛ፣ 3ኛ፣ 4ኛ እና 6ኛ ክስ ጥፋተኛ ባማድረግ በ5 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት፣

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2ኛ አመልካችን ደግሞ በ2ኛ፣ 3ኛ፣ 4ኛ፣ 6ኛና 7ኛ ክስ ጥፋተኛ በማድረግ በ15 ዓመት ፅኑ እስራት እና በብር 20000 / ሃያ ሽህ / መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

በአመልካቾች ይግባኝ አቅራቢነት ይግባኙን የተመለከተው የኮንታ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ተመልክቶ የአመልካቾችን የቅጣት ውሳኔ ብቻ በማሻሻል የስር 1ኛ ተከሳሽ በ5 ዓመት ጽኑ አስራትና በብር 10000 / አስር ሽህ / የገንዘብ መቀጮ፣ 1ኛ አመልካችን በ4 ዓመት ጽኑ እስራት፤ 2ኛ አመልካችን ደግሞ በ11 ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 20000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካቾች በድጋሚ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ከክስ 1-6 የተጠቀሱት ክሶች በአንድ በዛ ቢባል በሁለት ተጠቃለው መቅረብ የሚገባቸው መሆኑን፣ 7ኛ ክስም ቢሆን አመልካቾች ይህን ያህል ረዥም ዓመት ንግድ ፍቃድ ሳይኖራቸው ሲነግዱ መንግስት ያልተቆጣጠረበት ምክንያት ግልጽ አለመሆኑንና የክሱ አቀራረብ የህጉን ዓላማ ያልተከተለ መሆኑን፣ ቅጣቱን በተመለከተ ደግሞ የስር ፍ/ቤት እንደ ማክበጃ ተብለው የተያዙ ነጥቦች በአብዛኛው አመልካቾች ተከሰው ጥፋተኛ የሆኑበትን የህግ አንቀጾች ማቋቋሚያ ሆነው እያለ ዳግመኛ ማክበጃ መያዙ የወንጀል ህግ አንቀጽ 84/2/ ዓላማ ያልተከተለ መሆኑን፣ የአመልካቾችን ቅጣት ማቅለያ በአግባቡ ያልያዘላቸው መሆኑን በመግለጽ አመልካቾች እያንዳንዳቸው በ1 ዓመት ከ6 ወር እስራት እና የስር 1ኛ ተከሳሽና 2ኛ አመልካች ደግሞ እያንዳንዳቸው በብር 500 / አምስት መቶ / መቀጮ እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት የጥፋተኝነት ውሳኔውን በተመለከተ በከፍተኛ ፍ/ቤት የፀና በመሆኑ አልመለከትም ካለ በኋላ እገረ መንገዱን በማለት ተችቶ ቅጣትን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት የወንጀል ህጉን 88/2/ እና 179/ሐ/ በመጥቀስ ቅጣቱን አሻሽሎ በዘፈቀደ የስር ፍ/ቤትን የቅጣት ውሳኔ አግባብነት ሳይመዝንና ሳይተች ቅጣቱ ፍትሀዊ አይደለም ብሎ ማቅለሉ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያን እና አጠቃላይ የወንጀል ቅጣት ዓላማ እና ግብ ያልተከተለና አስተማሪ ያልሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው በማለት የስር የኮንታ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤትን የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ጥቅምት 02 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም የስር 1 ተከሰሽና 1ኛ አመልካች ከዚህ ክስ በፊት በኮንታ ልዩ ወረዳ ዓ/ህግ በቁጥር 3403 በቀን 08/09/2011 ዓ.ም በተጻፈ ክስ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና 438 ን ተላለፋችሃል ተብለው የጦር መሳሪያ በመያዝ የብርበራ ትዕዛዝ የያዙትን ፖሊሶች ስራቸውን እንዳይሰሩ ሀሰተኛ ወሬ በመንዛት የአካባቢው ሰው ገጀራና ጦር ይዞ እንዲወጣ በመንገር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ብርበራው እንዳይካሄድና በፖሊሶችና በመኪናቸው ላይ ጉዳት በማድረስ ወንጀል ተከሰው በመ/ቁ 17999 በቀን 22/11/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጥፋተኛ በማድረግ በ7 ዓመት ጽኑ እስራት የተወሰነባቸው መሆኑን፣ 1ኛ አመልካችና የስር 1ኛ ተከሳሽ በውሳኔው መሰረት ቅጣቱን እየፈጸሙ እያለ በድጋሚ 2ኛ አመልካችን ጨምረው በቀረበው የወንጀል ክስ ማመልከቻ ላይ ተጠቅሶ አልቀረበም በሚል ምክንያት የስር ፍ/ቤት ከ1-6 በጠቀሳቸው ክሶች ላይ በድጋሚ ተከሰው የተወሰነባቸው መሆኑንና፣ 2ኛ አመልካች ከ1-6 በተጠቀሱት ክሶች ላይ ጥፋተኛ መባሉ ከጥርጣሬ በላይ ባልተረጋገጠ ማስረጃ መሆኑን፣ 7ኛ ክስን በተመለከተ አመልካቾች ሱቅ እንደሌላቸው እና መኪኖች ሲያልፉ ህጻናት ሶፍትና ውሃ ሲሸጡ በማየት ነጋዴ ናቸው ማለቱ አግባብ አለመሆኑን ገልጸው የስር የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾች ፈጽመዋል በሚል በተለያዩ ወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ስር የተከሰሱበትን ክስ መሰረት በማድረግ የተሰጠው የትፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አግባብነት ከወንጀል ህግ አንቀጽ 61 እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ነጥቦች አንጻር ለመመርመር ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን የካቲት 25/2014 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው መልስ አመልካቾች የተከሰሱባቸው የወንጀል ድንጋጌዎች በአንድ ድርጊት ከሁለት በላይ የሆኑ ወንጀል ድንጋጌዎች በመጣስ ልዩልዩ ግዙፋዊ ውጤት የሚያስከትሉ ወንጀሎችን በአደገኛ ሁኔታ የጦር መሳሪያ ገጀራ፣ ጦር እና ድንጋይ በመያዝ የተፈጸሙ መሆናቸው በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ ይህን መሠረት በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት፡፡

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 61/1 ድንጋጌ በሕግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚደረጉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የወንጀል ድርጊቶች የተደረጉት በአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኛነት ሲሆን እና ድርጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈኑ ሲሆን አድራጊው ተመሣሣይ ባሕርይ ባላቸው በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች አይቀጣም በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 2 ድንጋጌም በሕግ በተጠበቀ በዚያው በአንድ መብት ላይ ተደጋግመው ወይም ተከታትለው የተደረጉ የወንጀል ተግባሮች በአንድ የወንጀል ማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኛነት እንደ አንድ ወንጀል የሚቆጠሩ መሆኑ፤ ወንጀል አድራጊው ለዚሁ እንደ አንድ ወንጀል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ለተቆጠረው እንጂ ተደጋግሞ ወይም ተከታትሎ ለተፈጸመው ለእያንዳንዱ ድርጊት የማይቀጣ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች ከ1ኛ እስከ 6ኛ ባሉት ክሶች ፈጽሙበት የተባለው የወንጀል ተግባር የአካባቢውን ጸጥታ ለመቆጣጠር የሄዱትን የፖሊስ አባላት በመደብደብ ስራ እንዳይሰሩ አድርገዋል፤ የፖሊስ አባለት ላይ ጥቃት ፈጽመዋል፤ ወታደራዊ ትዕዛዞች እንዲጣሱ አድርገዋል፤ ሌላውን ሰው አነሳስተዋል፤ በፖሊስ አባላት የሀሰት መረጃ አሰራጭተዋል፤ በወሬ ሕዝብን አሸብረዋል፤ የሀሰት ወሬ በማውራት ሕዝብን አነሳስተዋል የሚል ነው፤ ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 61(1)(2) ላይ እንደተገለጸው በአንድ የወንጀል ማድረግ ሐሳብ የተፈጸመ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል ማንም ሰው የጸና የንግድ ፈቃድ ሳይኖረው ንግድ ሲነግድ በተገኘ ጊዜ ተጠያቂ እንዲሚሆን አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49/2/ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ዓቃቤሕግ ይህንኑ መሠረት በማድረግ በ2ኛ አመልካች ላይ ክስ ያቀረበ ቢሆንም 2ኛ አመልካች ባቀረበው መከላከየ ማስረጃ ሱቅ እንደሌለው እና ባለቤቱ ድንች፣ ቅመማቅመምና በርበሬ ገበያ እየወሰደች የምትሸጥ መሆኑን አስረድቷል፡፡ ይህም የእለት ጉርስ ለማግኘት የሚፈጸም ተግባር መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዘሁ አግባብ 2ኛ አመልካች የቀረበበትን 7ኛ ክስ አስተባብሏል ማለት ሲገባው በፍርድ ትችቱ ላይ አመልካቾች ይህን ያህል ረዥም ዓመት ንግድ ፍቃድ ሳይኖራቸው ሲነግዱ መንግስት ያልተቆጣጠረበት ምክንያት ግልጽ አይደለም በማለት ያስቀመጠው ሀሳብ የሕጉን አላማ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ መሠረት በማድረግ በሥር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ማጽናት ሲገባው አመልካቾች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በተከሰሱበት እያንዳንዱ አንቀጽ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 34496 የካቲት 11 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

### <u>ትዕዛዝ</u>

- አመልካቾች የቅጣት ውሳኔ ከተላለፈባቸው ከነሐሴ 22 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ያለው ጊዜ ሲሰላ በዚህ ችሎት የጸናው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እያንዳንዳቸው በ1 ዓመት

ከ6 ወር እስራት እንዲቀጡ በማለት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ የፈጸሙ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ የሚመለከተው ማረሚያ ቤት አመልካቾችን በሌላ ጉዳይ የማይፈልጋቸው ከሆነ በዛሬው ዕለት ከእስር እንዲለቃቸው ታዟል፡፡ በትዕዛዙ መሠረት ማስፈጸም ይቻለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ይድረሰው፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም